# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

## የውሃ ምርት ሥርጭት፣ መስመር ዝርጋታ፣ ጥገናና ኦፕሬሽን ሥራዎች

## መምሪያ ቁጥር 10/2012

# መግቢያ

ባለስልጣኑ የከተማውን ነዋሪ የውሃ አቅርቦት ፍላጎት ለማርካት እና አሰራሩን ዘመናዊ ፣ቀልጣፋ ፣ ፍትሃዊ እና ከኪራይ ሰብሳቢነት የፀዳ ለማድረግ ስራዎች የሚከናወኑበትን ስታንዳርድ በማውጣት ዘርፈ ብዙ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ በመሆኑ፤

ይህም አላማ ግቡን ይመታ ዘንድ የስራ ክፍሎችን የስራ ተግባር ፣ ሃላፊነት በግልፅ በመለየት በማስቀመጥ የስራ መጓተት፣ የንብረትና የግዜ ብክነትን በማስቀረት እና የተለያዩ ዘርፎች እና የስራ ክፍሎች ተቀናጅተው እንዲሰሩ በማድረግ የውሃ ስርጭት መቆራረጥን መቀነስ በተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ተጣርቶ ወደ ከተማ የሚሰራጭ እና ገቢ የማይሰበሰብበትን ውሃ ለመቀነስ እና የውሃ ብክነትን ለመከላከል የሚረዳ የአሰራር ስርአት ለመዘርጋት በማስፈለጉ

በውሃ ምርት ስርጭት ፣ መስመር ዝርጋታ ፣ጥገና እና የኦኘሬሽን ሥራዎችን ግልፅ፣ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት ወጥ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት ስለታመነ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለስልጣን ውሃ ምርት ስርጭት፣ መስመር ዝርጋታ ፣ጥገናና አፐሬሽን ሥራዎች መመሪያ ቁጥር 10/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1. **"ባለስልጣን"** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ነው፡፡
2. **"ዋና ሥራ አስኪያጅ"** ማለት፡- የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡

3 **"ዘርፍ"** ማለት ፡-የባለስልጣኑ የውሃ አገልግሎት ም/ዋ/ሥራ አስኪያጅ ነው፤

4 **"አብይ የስራ ሂደት"** ማለት፡- በውሃ ዘርፍ ም/ዋ/ሥራ አስኪያጅ ሥር የውሃ አቅርቦትን በበላይነት የሚመራ የስራ ክፍል ነው፡፡

5 **"ንዑስ የስራ ሂደት"** ማለት ፡- በውሃ ዘርፍ ም/ዋ/ሥራ አስኪያጅ ሥር ባለው አብይ የስራ ሂደት ሥር ያለ ንዑስ ሥራ ክፍል ነው፡፡

6 **"ኬዝ ቲም" ማለት**፡- በውሃ ዘርፍ አብይ የስራ ሂደት ሥር ባለው ንዑስ ሂደት ሥር የሚገኝ የስራ ክፍል ነው፡፡

7 **"የውሃ ምርት "** ማለት ፡-ባለስልጣኑ ከገጸ ምድር እና ከርሰ ምድር የውሃ መገኛዎቹ ያገኘውና የአለም ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት መሰረት ተጣርቶና ታክሞ የቀረበ ለጤና ተስማሚ የሆነ ንፁህ ውሃ ነው፡፡

8 **"የገጸ-ምድር የውሃ መገኛ"** ማለት፡- ለግድቦች የዝናብ ውሃ በጐርፍ መልክ እንዲገባና እንዲከማች የሚያደርግ የግድቡ ተፋሰስ አከባቢ ነው፡፡

9 **"ከርሰ-ምድር ውሃ"** ማለት፡- ከጥልቅ ጉድጓድ ተቆፍሮ የሚወጣ ጥራቱን የጠበቀ ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭ ውሃ ነው፡፡

10 **"የውሃ ማጣሪያ ጣቢያ "** ማለት ፡- የአለም ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት መሰረት የገጸ ምድር ውሃ ክምችት የሚጣራበት ቦታ ነው፡፡

11 **"የውሃ ስርጭት"** ማለት ፡-ከየውሃ ምርት መገኛ ጣቢያዎች የሚገኙትን የውሃ ምርቶች ማሰራጨት ነው፡፡

12 **“ማጠራቀሚያ”** ማለት፦ ከማጣሪያ ጣቢያ የሚመጣው ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚከማችበት በከተማው ውስጥ በተለያየ ቦታ የሚገኝ የውሃ ማጠራቀሚያ ነው ።

13 **“ዲኤምኤ** /DMA/”District Metered Areas “ማለት፡- የሚገባውንና የሚወጣውን የውሃ መጠን ለማወቅ ከ500 እስከ 1000 ደንበኞችን በሚይዝ አካባቢ የተከለለ በቅ/ጽ/ቤቶች ገቢ የማይሰበሰብበትን የውሃ መጠን ለመቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስልት ማለት ነው።

14 **“ዞን/ሰብሲስተም “** ማለት፦ አንድ ሲስተም የውሃ መጠን የሚለካበት፣ለራሱ የግፊት መጠኑ የተወሰነበት፣ የተከለለ የውሃ ስርጭት አካባቢ ነው።

15 **“ከፍተኛ መስመር”** ማለት፦ ከማጠራቀሚያ ወደ ስርጭት ሲስተሙ ውሃ የሚተላለፍበት ስፋቱ ከ125 ሚ.ሜ እና በላይ የሆነ የውሃ መስመር ነው።

16 **“መለስተኛ መስመር”** ማለት፦ ከከፍተኛ መስመር ወይም ከማጠራቀሚያ ወደ ሲስተሙ ውሃ የሚያስተላልፍ ስፋቱ ከ125 ሚ.ሜ በታች የሆነ የውሃ መስመር ነው።

17 **“የጋራ መስመር ”** ማለት፡- ደንበኞች በራሳቸው ወጪ ያዘረጉትና ስፋቱ ከ 50 ሜ.ሜ በታች የሆነ መለስተኛ የውሃ መስመር ነው።

18 **“የግል መስመር ”** ማለት፡- ከባለስልጣኑ ወይም ከጋራ መስመር ላይ ተቀጥሎ ወደ ደንበኛው ቤት የተዘረጋ እና ሙሉ ኃላፊነቱ የደንበኛው የሆነ የውሃ መስመር ነው።

19 **“የውሃ መሰረተ ልማት“፡-** ማለት ማንኛውም የውሃ ምርት እና ስርጭት የሚከናወንበት ግድብ፣ ጉድጓድ፣ማጠራቀሚያ፣ ግፊት መስጭያ ጣቢያ ፣የውሃ መስመርና በላዩ ላይ የተገጠሙ መገጣጠሚያዎችና መሳሪያዎች እና ሌሎች ለውሃ ስርጭት እና ማጣራት የሚያገለግሉ ቁሶች ማለት ነው።

20 **“ዝቅተኛ ተጠቃሚ”** ማለት በወር ውስጥ እስከ 14 ሜትር ኩብ የሚጠቀም ደንበኛ ነው፣

21 **“መለስተኛ ተጠቃሚ”** ማለት በወር ውስጥ ከ 15-100 ሜትር ኩብ የሚጠቀም ደንበኛ ነው፣

22 **“ከፍተኛ ተጠቃሚ”** ማለት በወር ውስጥ ከ 100 ሜትር ክዩብ በላይ የሚጠቀም ደንበኛ ነው;

23 **“ተፋሰስ”** ማለት፦ ወደ ግድቡ የሚፈሱ ወንዞችና ምንጮች መገኛ ቦታ ነው።

24 **“ግድብ”** ማለት፣- ጥሬ የገፀ ምድር ውሃ ማከማቻ ነው።

## <u>አንቀጽ 3</u>
## <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ የሥራ መሪዎች እና ሠራተኞች፣ የመስመር ዝርጋታ ፣ቅጥያ፣ ጥገናና ኦፕሬሽን ሥራዎች በሚሰሩ የስራ ተቋራጮች ወይም ማህበራት እንዲሁም ከባለስልጣኑ የውሃ አገልግሎት ለማግኘት በሚጠይቁ እና አገልግሎቱን እያገኙ ባሉ ደንበኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ተግባርና ኃላፊነት
## አንቀጽ 4
## የውሃ ማጣራት፣ማምረት ማሰራጨትና ሲስተም ቁጥጥር ንዑስ የስራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት

**1. የተፋሰስ ጥበቃ ፣እንክብካቤ እና አስተዳደር**

1. የውሃ መገኛ ተፋሰስ አካባቢዎች ከኢንዱስትሪ፣ ከግብርና እና ከነዋሪዎች በሚፈጠሩ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች እንዳይበከል እንዲሁም የጥሬ ውሃን መጠን ሊቀንሱ ከሚችሉ የኢንቨስትመንት ወይም የልማት ስራዎች ለመታደግ በወር አንድ ጊዜ እና/ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው የመፈተሽ እና ተገቢው ቁጥጥር እንዲሁም የክልከላ እርምጃዎችን የመውሰድ እና የማስወሰድ ስራዎችን ያከናውናል ፡፡
2. ለብክለት አጋላጭ የሆነ ክስተት ከተገኘ በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል ብክለቱንም ያደረሰው አካል ተጠያቂ እንዲደረግ አስፈላጊውን መረጃ በማደራጀት ለህግ እና ኢንሹራንስ ደጋፊ የስራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡
3. በተፋሰስ አካባቢና በግድቦች ዙሪያ በየአመቱ የዛፍ ችግኞችን በመትከል፣ ያልተቋረጠ እንክብካቤ በማድረግ እና ሌሎች የመከላከያ ዘዴዎችን በመጠቀም ወደ ግድብ የሚገባውን የደለል መጠን በመቀነስ ከግድቦች የሚገኘው የጥሬ ውሃ ጥራት ደረጃ እንዳይቀንስ እና የኬሚካል አጠቃቀምም በአይነትና በመጠን እንዳይጨምር ጥረት ያደርጋል ፡፡
4. በንጹህ የመጠጥ ውሃ ማምረት ሂደት የሚፈጠሩ ዝቃጮች በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መንገድ መወገዳቸውን በመከታተል ጉዳት ሲከሰትም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
5. የተፋሰሶችን ከባቢያዊ ስነምህዳር ደህንነት በጋራ ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ የሚያስችል በአካባቢው ከሚኖሩ አርሶ አደሮች ፣ ከመንግስት አካላት፣ ከግል ባለኃብቶች እና ከባለስልጣኑ የተውጣጡ አባላት ያሉበት ፎረም በማደራጀት በተፋሰስ ዙሪያ በየሶስት ወሩ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ያወያያል የተፈጠሩ ስጋቶችን ያቀርባል ፣ የመፍትሄ ሃሳቦችን በማቅረብ የማወያየት እና የጋራ የማድረግ ሥራ በማከናወን የትግበራ ሂደቱን ይከታተላል ፡፡
6. የተፋሰስ አካባቢን ጽዱና አረንጓዴ ለማድረግ የሚረዱ እና የአካባቢውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ይሰራል፡፡

2. **የግድብና የማጣሪያ ጣቢያ ደህንነት ክትትል ቁጥጥርና አስተዳደር**

1. የግድቡን ደህንነት የሚከታተሉ የተለያዩ የጥበቃ እና የቁጥጥር መሣሪያዎች በትክክል የሚሰሩ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. በየእለቱ የግድብ ውሃ ከፍታ ፣ የሜትሮሎጂ መረጃ ፣ከግድቡ የዘለቀ ውሃ, /dam seepage/ በመከታተል መረጃዎችን በመሰብሰብ ፣ በማደራጀት፣ በመተንተን መወሰድ ካለበት የመፍትሔ ሃሳብ ጋር አጠናቅሮ ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል፡፡
3. በግድቡ ላይ የተገጠሙ የኤሌክተሮ መካኒካል መሳሪያዎችን የማጽዳት፤ የመፈተሽ ፤ ግሪስ የማድረግ ፣የግድብ ውሃ የመክፈት እና የመዝጋት ፣የተከማቸውን ደለል የማስወገድ እና ግድቡ ሞልቶ ሲፈስ /overflow/ በመከታተል የማስተንፈስ ሥራ ይሰራል፡፡
4. ባዕድ ነገር ወደ ግድቡ እንዳይገባና የውሃ ጥራት ደረጃ እንዳይቀንስ ለማድረግ እንዲሁም የማጣሪያ ጣቢያዎችን ደህንነት ለመጠበቅ እንዲቻል የተጠናከረ የጥበቃ እና የፀጥታ ክትትል ያደርጋል፣
5. በጥሬ ውሃ ላይ የሚደረግን የጀልባ ላይ ጉዞ የኦፕሬሽን ተግባር ያከናውናል ያስተዳድራል፡
6. ለውሃ ማምረት የሚያገለግሉ ፡-
   ሀ. የማጣሪያ መደቦችን /Filter bed/ በተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የማጠብ፣
   ለ. የክላሪፋየር ገንዳዎች በትክክል መሰራታቸውን ማረጋገጥ ፣
   ሐ. የደለል ማዝቀጫ ገንዳዎች እና የተገጠሙ መሳሪያዎች ጽዳት መጠበቅ እና በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ ፣ሲበላሹም የማስጠገን እና ወይም የመጠገን እንዲሁም የመቀየር ተግባር ያከናውናል፡፡
   መ. በውሃ ማጣሪያ ጣቢያዎች ያሉትን የመጠባበቂያ ጀነሬተሮች ለሥራ ዝግጁ የማደረግና የነዳጅ አቅርቦቱ እንዳይስተጓጎል የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡

3. **የውሃ ምርት ጥራት ቁጥጥርና ምርመራ**

1. **የግድብ ጥሬ ውሃ ጥራት አጠባበቅ**

አልጌ ግድቡ በያዘው ውሃ ላይ በማበብ በመጠጥ ውሃ ጣዕም፣ ሽታ እና ጥራት ላይ ተጽዕኖ እንዳያስከትል በየጊዜው ክትትል በማድረግ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ እና መጠን ኬሚካል ይረጫል፣

2. **የገጸ ምድር ውሃ ምርት ጥራት**

ለውሃ ምርት የማጣራት ሂደት የሚያስፈልጉ የኬሚካል አይነቶችን በተሰጠው መስፈርት መሰረት ውህደቱ የተሠራ መሆኑን በመከታተል የተጣራው ውሃ የአለም ጤና ድርጅት ያወጣውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

3. **የከርሰምድርውሃ ምርት ጥራት**

ከጉድጓዶችና ከምንጮች ወደ ማጠራቀሚያ የሚገባ ውሃ መታከም የሚገባው በመሆኑ ውሃውን ለማከም የአገልግሎት ላይ የሚውለውን የኬሚካል መጠን በመወሰን እና በማከም፣ በተወሰነው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ናሙና በመሰብሰብ ችግር ከተገኘ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ጥራቱ የአለም ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፣

4. **የማጠራቀሚያ ጋኖችና የውሃ መስመር ጥራት አጠባበቅ**

1. ለውሃ ስርጭት አገልግሎት የሚውሉ የውሃ ማሰራጫ መስመሮችና ማጠራቀሚያዎች በተለያየ ምክንያት ብክለት እንዳይከሰትባቸው ተከታታይ ክትትል በማድረግ የሚሰራጨው የመጠጥ ውሃ የአለም ጤና ድርጅት ያወጣውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. ለህብረተሰቡ የሚቀርበው የተጣራ የመጠጥ ውሃ ብክለት እንዳይደርስበት የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖች፣ የውሃ ማሰራጫ መስመሮች ፣በአዲስ መልክ ወደ ውሃ ስርጭቱ የሚገቡና እንደዚሁም ጥገና ተደርጎላቸው አገልግሎት መስጠት የሚጀምሩ የውሃ ስርጭት መገልገያዎች በሙሉ የኬሚካሉን መጠንና አይነት በመወሰን ወደ ስርጭት ሲስተም ከመግባታቸው በፊት ታጥበው እንዲታከሙ በማድረግ ከብክለት የጸዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. ወቅታዊ የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖችን የማጠቢያ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ መተግበሩን በመከታተል ክፍተት ካለም እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል
4. በዋና ዋና/ ከፍተኛ/ የውሃ ማስተላለፍያ መስመሮች ብክለት እንዳይከሰትባቸው አመታዊ የክትትል እና የጥበቃ ዕቅድ በማውጣት የማጠብና የማከም ስራዎችን ያከናውናል፡፡

5. **ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚደርሰው ውሃ ጥራት ቁጥጥር**

1. በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከተቋማት፣ ከደንበኛ ቤቶች እና ከቦኖዎች ናሙና በመሰብሰብና በመመርመር ብክለት ካጋጠመም ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ለደንበኞች የሚደርሰው የመጠጥ ውሃ የአለም ጤና ድርጅት ያወጣውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. ከተጠቃሚ የሥራ ዘርፎች ወይም ከደንበኛው የውሃ ጥራት ምርመራ ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊውን ሳምፕል በመውሰድ በሁለት ቀን ውስጥ ውጤቱን ያሳወቃል ብክለት ከተገኘም የማስተካኪያ እርምጃ ይወስዳል፣

3. የውሃ ጥራት ምርመራ እንዲደረግላቸው ለሚጠይቁ የውጭ ደንበኞች (የከርሰ ምድር ውሃ ለግል ጥቅማቸው ያስቆፈሩ ድርጅቶች ፣ግለሰቦች፣ ውሃ በማምረት አሽገው ለሚያቀርቡ ድርጅቶች ) የውሃ ጥራት ምርመራ ሥራዎች ያከናውናል፡፡
4. የውሃ ወለድ በሽታ ከተከሰተ ከጤና ጽ/ቤት እና ከጤና ተቋማት ጋር ጥብቅ የመረጃ ልውውጥ በማደረግ የበሽታውን ምንጭ ለማወቅ የሚሰራን ስራ ይተባበራል፡፡

6. **በውሃ ማጣራት ሂደት የተለየውን ዝቃጭ ማጣራትና ማስወገድ**

1. የዝቃጭ ውሃ ማጣሪያ ኬሚካል ውህድት መጠንን የመከታተል፣ የዝቃጭ ውሃ ማጣሪያ ኬሚካል መበጥበጫ ገንዳን የማጽዳት፤የዝቃጭ ኬክ ማምረቻ ማጣሪያ መሳሪያ Filter press / ዝቃጭ ማጥለያ መሳሪያ/ የማጠብ እና የኤሌክተሮ መካኒካል መሳሪያዎችን የማጽዳትና ግሪስ የማድረግ ስራዎችን ያከናውናል፡፡
2. ተጣርቶ የሚወጣውን የዝቃጭ መጠን አካባቢውን እንዳይበክል ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ያስወግዳል ፣

7. **ለውሃ ማጣሪያ የሚረዱ መሳሪያዎችና ኬሚካሎች አያያዝ፣ እንክብካቤ እና ክትትል**

1. የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን ደህንነትና አያያዝ ስርአት ያወጣል ተግባራዊም ያደርጋል፣
2. የአገልግሎት ጊዜአቸው ያለፈ ለውሃ ማጣሪያ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን ያስወግዳል እንዲሁም የማጣሪያ ኬሚካሎች ክምችት ማነስ ሲያጋጥም እንዲሟላ ያደርጋል፣
3. በአገልግሎት ላይ የዋለውን ባዶ የክሎሪን መያዥያ ሲሊነደር በተገቢው ቦታ መከማቸቱን እና በውስጡ ምንም ክሎሪን የሌለ መሆንኑን በመፈተሽ የአካባቢው ደህንነት እንይበክል ያደርጋል፡፡
4. ኬሚካል የያዙ ሲሊንደሮች ደህንነት እና የተቀመጡበትን ቦታ ለአደጋ የተጋለጠ አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡
5. ውህድ ክሎሪን ለማምረት የሚስፈልግ ዓመታዊ የግብዓት ፍላጎት እና የግዥ ሰነድ በማዘጋጀት የግዥ ሂደቱን የመከታተል እና የመደገፍ ሃላፊነት አለበት፡፡
6. ውህድ ክሎሪን በማምረት ወደ ማጣሪያ ጣቢያው ሲስተም የማስራጨት ፣የኦፕሬሽን ደህንነት የመከታተል እና የመቆጣጠር ተግባር ያከናውናል፡፡
7. በኤሌክትሮ ክሎሪኒሽን ሲስተም ላይ የተገጠሙ የኤሌክትሮ መካኒካል ፣ሃይድሮሊክ እና ኤሌክትሮኒክስ መሳሪዎችን ፅዳት ፣ሰርቪስ እና ቀላል ጥገና ስራዎችን ያከናውናል፡፡

8. **የውሃ ምርት ጥራት ምርመራ እናመረጃ አሰባሰብ**

1. በየቀኑ ወደ ምርት የገባውን ጥሬ የውሃ መጠን፣ የፈጀውን የኬሚካል አይነትና መጠን እና ተመርቶ ወደ ስርጭት የገባውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ መጠን መረጃ በየቀኑ መዝግቦ በመያዝ ወደ መሀከላዊ መረጃ ቋት ይልካል።
2. የአለም ጤና ድርጅት የውሃ ጥራት ደረጃ፡ የፌደራል ጤና ጥበቃን የውሃ ጥራት ደረጃ እና የከተማውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ ከሁሉም የውሃ መገኛዎች  ቢበዛ በየሣምንቱ ናሙና በመውሰድ የኬሚካል፣ ፊዚካል እና ባክትሮሎጂካል ምርመራ በማካሄድ መረጃውን በማደራጀት እና በመተንተን በየሣምንቱ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና ለመሀከላዊ መረጃ ቋት ይልካል ፡፡
3. የአለም ጤና ድርጅት የውሃ ጥራት ክትትል ደረጃ፣ የፌዴራል ጤና ጥበቃን የውሃ ጥራት ደረጃ እና የከተማውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ በየቀኑ ከስርጭት መረብ ውስጥ፣ ከውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖች፣ ከደንበኞች ቅጥያ ናሙና መውሰድ  እና ምርመራ በማካሄድ መረጃውን በማደራጀትና መተንተን ለመሀከላዊ መረጃ ቋት በየቀኑ ሪፖርት ይልካል።
4. የውሃ ጥራት ለመጠበቅና ለላብራቶሪ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ኬሚካሎች አቀማመጥ፣ መጠን እና በግ/ቤት ያሉ ኬሚካሎች ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያገለግሉ መረጃ በማደራጀትና በመተንተን በየወሩ ለውሃ ማ/ማ/ሲ/ ቁ/ ን/ የሥራ ሂደት ሪፖርት ይልካል።

## <u>አንቀጽ 5</u>
## <u>የከርሰ ምድር የውሃ ምርት</u>

### 1. የከርሰ ምድር የውሃ ምርት መገኛ ጣቢያዎች  ክትትልና አስተዳደር

1. ከከርሰ ምድር የውሃ ምርት መገኛዎችና ከዌል ፊልዶች፣ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ በተለያየ ቦታ ከተቆፈሩ ጉድጓዶችና ምንጮች የሚገኘውን የውሃ ምርት አቅርቦት ሥራዎችን ለማሳለጥ አስፈላጊውን ዕቅድና በጀት ማዘጋጀትና አፈጻጸሙን መከታተል አለበት፣
2. የከርሰ ምድር የውሃ ምርት መሳሪዎችን /(Hydraulic and Electro mechanical) / በፕሮግራም የቅድመ ብልሽት መከላከልና  ጥገና እንዲከናወንላቸው  መደረግ  አለበት፣
3. ከጉድጓዶች እና ምንጮችን የሚመረተው የውሃ ምርት ታክሞ መስራጨቱን መቆጣጠርና መከታተል አለበት፣
4. የከርሰ ምድር የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖች  በየአመቱ በሚዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መታጠብ እና መታከማቸውን ይከታተላል።
5. የውሃ ማከሚያ ኬሚካል ክምችት በበቂ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥና የተበላሹ የኬሚካል ውህደት መሳሪያዎች በጊዜው እንዲጠገኑ ወይም እንዲቀየሩ ማድረግ አለበት።

6. የከርሰ ምድር የውሃ መገኛዎች ላይ የተገጠሙትን የኃይል አቅርቦት መጠባበቂያ ጀነሬተሮችን በመረከብ ፤ማስተዳደርና ደህንነታቸውን መጠበቅ ፣ ችግር ካለ ለሚመለከተው አካል አሳውቆ ማስጠገን ፤ የነዳጅ ፍጆታን በመከታተል የነዳጅ አቅርቦት ጥያቄ በወቅቱ እንዲቀርብ መደረግ አለበት፣
7. የከርሰ ምድር የውሃ መገኛዎች ውስጥ ያሉትን ጠላቂ ፓምፖች፣ የኤሌትሪክ ቦርዶችና ለውሃ ስርጭቱ ማሳለጫ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ደህንነታቸውንና ንጽህቸውን መጠበቅና መከታተል አለበት።
8. በየጊዜው የጉድጓዶችን የመዳረሻ መንገድ ጥገና፣የጥበቃና ፓናል ቦርድ ቤት ፣ በጉርፍ የሚጠቁ ጉድጓዶችን የመከላከያ ሥራ እና ፣ የጉድጓዶች/Well head /ጥናት በማስጠናትና በጀት በማስያዝ የማስተካከያ ሥራ መሰራት አለበት።
9. ጉድጓዶችና ምንጮች በተዘጋጀዉ የጊዜ ሰሌዳ፣ በዕቅድ፣ መስፈርት እና በጀት መሰረት መጠረጋቸውን ይከታተላል ፣
10. በማጠራቀሚያዎችና በጉድጓዶች ይዞታ ውስጥ ያሉ የውሃ መስመሮች ላይ ጉዳት ሲደርስ ወዲያዉኑ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በማሳወቅ መጠገኑን ይከታተላል።

## 2. የከርሠ ምድር ውሃ ክትትል (Monitoring) እና መልሶ ማጐልበት

1. በዌል ፊልዶች ደረጃ ለምተው በሚገኙ ጣቢያዎች እና አካባቢ/ Catchment area/ የከርሠ ምድር ውሃ ብክለት እንዳይፈጠር ያሉበትን ሁኔታ በማጥናት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል።
2. በዌል ፊልዶች ላይ የ Ground Water Model እንዲሠራ በማድርግ፣በየጊዜው የሞዴሉን Calibration & Post Auditing በመስራት አስፈላጊው ማስተካከያ ያደርጋል።
3. በዌል ፊልዶችና ከተማ ውስጥ በተቆፈሩ ጉድጓዶች ላይ የከርሠ ምድር ውሃ ከፍታ / Ground water level /እና ውሃ ጥራት /Quality / ጥናት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል።
4. መደበኛ እና ተከታታይነት ያለው የውሃ ምርት እና ጥራት ክትትልን መሰረት ያደረገ የጠረጋ /Rihabilitation/ ተግባር በማዘጋጀት ሂደቱን ይከታተላል።

## 3. የከርሰ ምድር የውሃ ምርት መረጃ አሰባሰብ

1. በማምረት ሂደት አስፈላጊ ግብአቶች መሟላታቸውን በመከታተል የእለቱን የውሃ ምርት፣ የማጣሪያ ኬሚካል መጠን ፍጆታ እና ጉድጓደቹ የሰሩበትን ሰዓት በመሰብሰብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ አደራጅቶ በመያዝ መረጃዎቹን ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ ይልካል።

2. የከርሰ ምድር የውሃ ምርት ክትትል መሳሪዎችን (የስካዳ ሲስተም፣ ሬድዮ እና ስልክ) ተረክቦ ደህንነታቸውን በመጠበቅ ለታለመላቸው አላማና በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ፣መልዕክት በመቀበልና በመስጠት ለሚመለከተው የስራ ክፍል መረጃ ያስተላልፋል፡፡
3. ለውሃ አቅርቦት የሚቆፈሩ ጉድጓዶችን በቁፋሮው ወቅት የተገኙ መረጃዎችን፣በውስጣቸው የተተከሉ ጠላቂ የውሃ ፓምፖች መረጃን ከነ ካታሎጉ፣ያሉበትን ቦታ /x,y,z/ ፣ከጉድጓዶቹ የሚገኘው የውሃ ምርት የሚደርስበት ማጠራቀሚያ ወይም አካባቢ፣ የተቆፈሩበት ዘመን፣ የመንገድና የጥበቃ ሁኔታ እና የመሳሰሉትን መረጃዎችን አሰባስቦ በመያዝ ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ መላክ አለበት ፣
4. የየለቱን ፣የሳምንቱን፣የወሩን የውሃ ምርት መጠን፣ ሃይል ፍጆታና የመብራት ሀይል መቆራረጥ የተከሰተበትን ሰዓት፣ጀነሬተሮች የሠሩበትን ሰዓት እና የነዳጅ ፍጆታ መረጃዎች ከየጣቢያዎቹ በማሰባሰብ አደራጅቶ በአግባቡ በመያዝ ትክክለኛነቱን አረጋግጦ መረጃውን ለሚፈልገው የስራ ክፍል እንዲሁም ለመዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ ይልካል፡፡
5. በተለያዩ ምክንያቶች ጉድጓዶቹ ሙሉ ለሙሉ ምርት በማይሰጡበት ወቅት መረጃዉን በማጠናቀር ለመዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ ይልካል፡፡

## አንቀጽ 6

## ኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎችና የጀነሬተር ጥገናና ተከላ

### *1. ኤሌክትሮ መካኒካልና የጀነሬተር ግብአት አቅርቦትና አያያዝ*

1. የውሃ ስርጭቱን ለማዳረስ የግፊት መስጫ ፓምፕ የሚያስፈልግ ከሆነ በጥናት የተደገፈ የዕቃዎቹን ዝርዝር መስፈርት የያዘ ሰነድ ያዘጋጃል፣ በሰነዱ መሠረትም የኤሌክትሮ መካኒካል መሣሪያዎት እንዲገዙ በጀቱን በማፀደቅ ግዥ እንዲፈፀም ይጠይቃል ለግዥ ሂደቱም ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
2. በአገልግሎት ዘመንና በጥገና ምልልስን ምክንያት ሊተኩ የሚገባቸውን የኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎች እንዲገዙ መስፈርቱን አዘጋጅቶ በጀት በማስያዝ ግዥ እንዲፈፀም ይጠይቃል፡፡የግዥ ሂደቱም እንዳይጓተት ከሚመለከተው ክፍል ጋር በቅርበት በመደጋገፍ እና ጠንካራ ክትትል በማድረግ በወቅቱ ግዥው እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡
3. በጥናት የተደገፈ ዝርዝር መስፈርቶችን በማዘጋጀት እና በጀት በማስያዝ የስካዳ ሲስተምና እና የሬዲዮ መገናኛ መሳሪያ ግዥ ይጠይቃል፡፡

4. የመጠባበቂያ ጀነሬተሮችን በመትከል ደህንነታቸውን በመጠበቅ እና/ወይም ሌሎች አማራጭ የሃይል አቅርቦቶችን በማጥናት ወይም በማስጠናት በሃይል መቆራረጥ ምክንያት የሚከሰተውን የውሃ ምርትና ስርጭት መቆራረጥ ችግር ይቀንሳል፡፡
5. የውሃ ስርጭቱን ለማድረስ የመጠባበቂያ የኤሌክትሮ መካኒካል እና ጀነሬተሮች ፍላጎት በጥናት የተደገፈ ዝርዝር መስፈርት አዘጋጅቶ በጀት በማስያዝ ግዥ ይጠይቃል ፣ የግዥውን ሂደትም በመከታተል  የቴክኒክ ጉዳዮቹን ይደግፋል፡፡
6. በየወቅቱ አስፈላጊ የሆኑ የኤሌክትሮ ሜካኒካል መሳሪያዎች መለዋወጫ እና መጠባበቂያ ዕቃዎችን ዝርዝር መስፈርት በማዘጋጀት በጀት በማስያዝ ግዥ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ በመጠባበቂያ የተያዘን መለዋወጫ ለመጠባበቂያው ከሚያዘው በላይ ትርፍ ካልሆነ በቀር ለሌላ አካል በብድር/በትውስት …ለመስጠት አይቻልም፡፡

## 2. ኤሌክትሮ መካኒካል መሣሪያዎች  ተከላ፣ አያያዝ፣ ቅየራና ጥገና

1. ማንኛቸውም የኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎች በዲዛይኑ መሰረትና በጥናቱ ላይ በተጠቀሰው ቦታ ላይ የትግበራ ስታንዳርድን ሳያዛባ ይተክላል፡፡
2. ማንኛውም የኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎች ሚመለከታቸው ዘርፍ ሳይፈቀድ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር እና/ ወይም ፈቶ ለመለዋወጫነት መጠቀም አይቻልም፡፡
3. አስፈላጊ ሲሆን የኤሌክትሮ መካኒካል እና ጄኔሬተር ዕቃዎች አቅርቦት ጥገና እና ተከላ ስራዎችን በሶስተኛ ወገን ያሰራል፡፡
4. በሶስተኛ ወገን የሚሰሩ የኤሌክተሮ መካኒካል እና ጄኔሬተር ዕቃዎች አቅርቦት ጥገና እና ተከላ  ሥራዎችን ጥናት፣ ዲዛይን፣ የሱፐርቪዥንና የኮንትራት አስተዳደር ስራዎችን ያከናውናል ፤ በየግፊት መስጪያ ጣቢያዎች የተተከሉ ፖምፖችና ሞተሮች ፣ በየጉድጓዱ የገቡ ጠላቂ ፓምፖችን ይከታተላል ፣ ይጠግናል ፣ ሌሎች  ችግሮች  ካሉም  መፍትሄ ይሰጣል፡፡
5. በተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎች የአሰራር ሁኔታ  መረጃ መሰብሰብና በመተንተን መሳሪያዎችን በመፈተሽ በውሃ ሲስተም ማሳለጫ መሳሪያዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን አስቀድሞ በመተንበይ የቅድመ ብልሽት ፍተሻና ጥገና / Preventive maintwnance/ በማድረግ  የውሃ አቅርቦት እንዳይስተጓጎል  ያደርጋል፡፡
6. የተለያዩ መጠን ያላቸው የውሃ መስመሮችን እና የኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎችን ከሚመለከተቸው የስራ ክፍሎች  ጋር በመቀናጀት  የብየዳ ሥራዎችን  በመስክም ሆነ በወርክ ሾፑ  ይሰራል፡፡
7. የአስካዳ ሲስተም እና የሬዲዮ መገናኛ መሳሪያዎችን ተከላ፤ ቀላል፣ መካከለኛና ከፍተኛ ጥገናና እንክብካቤ  እና የቅድመ ብልሽት የመከላከል ሥራዎችን  ያከናውናል፡፡

8. በኤሌክትሮ መካኒካል መሣሪያዎች ላይ ከሥራ ሰዓት ውጭ የውሃ ምርትና ስርጭትን የሚያስተጓጉል ችግር ከተከሰተ መረጃው ሲደርስ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አስቸኳይ ጥገና በማድረግ አገልግሎቱ እንዲጀምር ያደርጋል፡፡
9. አዲስ ለሚገቡ ቴክኖሎጅዎች (የኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎች)፣የውሃ ቆጣሪ መመርመሪያ ማሽን፣የኤሌክትሮ መካኒካል ፍሎው ሜትር ተከላ እና የመሳሰሉት መሳሪያዎች ቀላል፣ መካከለኛና ከፍተኛ ጥገና እንዲሁም እንክብካቤ ሥራዎችን ያከናውናል፡ ፡

***3. የጀነሬተር ተከላ፣ ጥገናና አስተዳደር***

1. የመጠባበቂያ ጀነሬተሮች እንዲተከልላቸው በሚጠይቁ የስራ ክፍሎች ፍላጎት ላይ በመመስረት ጥናት በማካሄድ በየውሃ ግፊት መስጭያ ጣቢያዎችና ጉድጓዶች የተከላ ሥራ ያከናውናል፡፡
2. በስራ ላይ ያሉ ጀነሬተሮችን በመከታተል የቅድመ ብልሽት ፣ የድንገተኛ የጥገና በእቅድ ላይ የተመሰረተ የሰርቪስ እና የደህንነት እንክብካቤ ስራዎችን ያከናውናል፡፡
3. በተለያየ ቦታ ለተተከሉ የባለስልጣኑ ጀነሬተሮች ነዳጅ፤ ዘይትና ቅባት ግዜውን ጠብቆ ( ጀነሬተሮቹ ስራ ከማቆማቸው ወይም በታንከራቸው የያዙትን ከመጨረሳቸው በፊት) የማቅረብና ስለአጠቃቀሙም ተገቢው ክትትል ያደርጋል፡፡
4. ለጀነሬተር ኦፕሬተሮች የኦፕሬሽን አጠቃቀም ማንዋል በማዘጋጀት ስልጠና ይሰጣል፡፡

***4. ኤሌክትሮ መካኒካል መሣሪያዎች እና ጀነሬተር መረጃ አሰባሰብ***

1. በከተማው ውስጥ ባሉ የግፊት መስጭያ ጣቢያዎች የሚገኙትን ፓምፕና ሞተር፣ ጄኔሬተር፣ በጉድጓዱ የተተከሉ ጠላቂ ፓምፖች አይነት እና የተተከሉበትን ቦታ የሚገልፅ ሙሉ መረጃ /ካታሎግ አስካን በማድረግ፣ የተተከሉበትን ቦታ/x,y,z/ ፣የሚገፋው ውሃ የሚደርስበትን ቦታ በመረጃ ማሳባሰቢያው መስፈርት መሰረት አሰባስቦ በመያዝ ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ ይልካል፡፡
2. በውሃ ምርት እና የግፊት መስጭያ ጣቢያ የሚገኙ የኤሌክትሮ መካኒካልና ሃይድሮሊክ መሳሪያዎችን ሁኔታ በስታንዳርዱ መሰረት በየጊዜው ክትትል በማድረግ ወቅታዊ መረጃዎችን ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ይልካል፡፡
3. የኤሌክተሮ መካኒካልና ሃይድሮሊክ / As Bulit Drawning/፣ የጥገና እና ኦፕሬሽን ማንሆሎችን /parts machial /ካታሎግ ፤ወዘተ በሃርድና በሶፍት ኮፒ አደራጅቶ ይይዛል፡፡
4. የሁሉንም ጀነሬተሮች ወቅታዊ መረጃዎች በማጠናቀር ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ይልካል፡፡

## አንቀጽ7

## ውሃ መስመር ጥናት ፣ ዲዛይን ፣ዝግጅትና ቁጥጥር ንዑስ የስራ ሂደትተግባርና ኃላፊነት

### 1. የውሃ መስመር ጥናትና ዲዛይን ዝግጅት

1. የውሃ አገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የተደገፉ አሰራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዲዛይና ሰነዶችን ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፡፡
2. የውሃ አገልግሎት ለሚሰጥባቸው እቃዎች ፣አገልግሎቶች ፣ግንባታዎችና ለግንባታ ለግብአቶች የሚያገለግል ቋሚ ቢ.ጋር/TOR/፣ የጨረታ ሰነድ ፣ መስፈርት/ Specification/ እና ካታሎግ ያዘጋጃል፤ በየግዜውም አዳዲስ ነገሮች ሲፈጠሩ ወይም ለውጥ ሲኖር ጥናት በማድረግ ወቅታዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
3. አዲስ የውሃ አቅርቦት ለመስጠት ለሚታሰብበት ወይም ዕቅድ ለተያዘበት ለከተማው የማስፋፊያ አካባቢዎች እና/ወይም የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ሪልስቴት፣ኢንዱስተሪ መንደርና ሌሎች የስራ ፣የመኖሪያ እና ማህበራዊ ተቋማት ወዘተ የሚኖረውን የውሃ ፍላጐት፣ የውሃ አቅርቦት ሁኔታ ፣ የውሃ ስርጭት ሲስተም ፣የተጠቃሚ ብዛት ፣የግንባታው አይነት እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮግራሞችን መረጃ ይሰበስባል ፤ይተነትናል ያደራጃል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 በሰበሰበው መረጃ እና በባለስልጣኑ ስታንዳርድ መሰረት ለነዚህ አካባቢዎች የሚሆን የውሃ መስመር ዝርጋታ ጥናት፣ ዲዛይን እና አስፈላጊ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ የመስመሩ ዝርጋታም በጥናቱ መሰረት መሰራቱን ይከታተላል ያረጋግጣል፡፡
5. በዋናው መስሪያቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለውሃ አገልግሎት ለሚሰሩ አነስተኛ ግንባታዎች ፣ለውሃ መስመር ዝርጋታ፣ ጥገና፣ ቅየራና ቅጥያ የሚያስፈልጉ ዲዛይንና የአሰራር የጥራት ደረጃዎች (ስታንዳርድ) በማዘጋጀት ሥራ ላይ ያውላል፡፡
6. የከፍተኛ እና መለስተኛ የውሃ መስመሮች ጥናት፤ ዝርጋታ፤ቅየራና ቅጥያ በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት እየተከናወኑ መሆናቸውን ይከታተላል በየግዜውም አፈጻጸማቸውን የመገምገም ስታንዳርዶችን የመከለስ ሥራ ያከናውናል፡፡
7. በሶስተኛ ወገን /በኮንትራት/ ለሚሰሩ ለውሃ አገልግሎትየሚውሉ የግንባታ ስራዎችን ኮንትራት ያስተዳድራል፤ ሥራዎቹም በተቀመጠው ዲዛይንና መስፈርት መሰረት መሰራታቸውን ይቆጣጠራል፤ ከስራው ጋር የተያያዙ ጉዳዮቹን መፍትሄ ይሰጣል፡፡
8. ለውሃ ዘርፍ በጨረታ ለሚገዙ እቃዎች ፣አገልግሎቶችና ግንባታዎች የቴክኒክ ግምገማ እና ኢንስፔክሽን ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## 2. የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ቅየራና ክትትል ተግባራት አፈጻጸም

1. አዲስ ፣ቅየራ፣ ማዛወሪያ ወይም ማሻሻያ የሚስፈልጋቸው የመንግስት መጋቢ መስመሮች የጥናት ዲዛይን እና የእስፔሲፊኬሽን በማዘጋጀት በሚመለከታቸው አካላት በማስተቸት ሲፀድቅ ለግንባታ ዝግጁ መደረግ አለበት፡፡
2. በበጀት አመቱ ለሚዘረጋ የከፍተኛም፣ መለስተኛ እንዲሁም የቀላል (የደንበኛ) የውሃ መስመር ቧንቧ፣ መገጣጠሚያ ና ለውሃ ስርጭት መሳለጥ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች በቂ ክምችት መኖሩን መረጋገጥ አለበት፡፡
3. የሚዘረጋውና የሚቀየረው የውሃ መስመር ተዘጋጅቶ በጸደቀው ጥናትና ዲዛይን መሰረት መሆን አለበት፣
4. ባለስልጣኑ እሰከ ደንበኛው ቤት 12 ሜትር ርቀት ድረስ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚያጓጉዝ የውሃ መስመር ለመዘርጋት እና ለመቀየር አስፈላጊውን ወጭ መሸፈን አለበት፣
5. የዋናው መስሪያቤት የከፍተኛ የውሃ መስመር ስፋታቸው 125ሚ.ሜ እና ከዛ በላይ የሆኑትን የውሃ መስመር መዘርጋት፣ መቀየር፣ መንከባከብ እና ማስተዳደር አለበት ፣
6. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቧንቧ ስፋታቸው ከ110 ሚ.ሜ እና በታች የሆኑትን መለስተኛ እና ዝቅተኛ የውሃ መስመሮችን መዘርጋትና መቀየር ፣መንከባከብ እና ማስተዳደር አለበት ፣
7. ለመስመር ግንባታና ጥገና የሚወጣው የግንባታም ሆነ የጥገና እቃ የውሃ መስመር ዝርጋታ ወይም ጥገናው እንደተጠናቀቀ ወይም በተለያየ ምክንያት ሥራው ከ15 ቀን በላይ ከተቋረጠ፣
   - ሀ.የከፍተኛ መስመር ከሰባት /7 ቀን/ በላይ በግንባታው ወይም በጥገናው ቦታ ላይ መቆየት የለበትም፣
   - ለ. የመለስተኛ መስመር ከሶስት /3 ቀን /በላይ በግንባታው ወይም በጥገናውቦታ ላይ መቆየት የለበትም፣
   - ሐ.የቀላል መስመር ከአንድ/1ቀን/በላይ በግንባታው ወይም በጥገናው ቦታ ላይ መቆየት የለበትም
8. ለመስመር ዝርጋታ ወይም ጥገና የወጡ የግንባታም ሆነ የጥገና እቃዎች ስራው በተጠናቀቀበት የከባድ መስመር በሰባት/ የመካከለኛ በሶስት ቀናት እና የቀላል መስመር በ1 ቀን ውስጥ ተራፊ ንብረቱ በርክክብ ሰነድ ተመላሽ መደረግ አለበት ፡፡
9. ባለስልጣኑ የከፍተኛ እና የመለስተኛ የውሃ መስመሮችን ዲዛይን እና ዝርጋታ ሥራን በሶስተኛ ወገን ሊያሰራ ይችላል ሆኖም በሶስተኛ ወገን የሚሰሩ ሥራዎች የግንባታን እና የዲዛይን ስራ ቁጥጥር በባለስልጣኑ መሰራት አለበት ፣
10. የውሃ ብክለት እንዳይኖር በመንገድ የጎርፍ ውሃ መሄጃ ቦይ ወይም በቆሻሻ መድፊያ አካባቢዎች ውስጥ የተዘረጉ የውሃ መስመሮች ሁሉ እየተፈተሹ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ተነስተው በተገቢው ቦታ መዘርጋት አለባቸው፡፡

11. የሚዘረጋው እና የሚቀየረው  የውሃ መስመር ከከተማው ማስተር ፕላን ጋር የተጣጣመ እና በከተማው ውስጥ ካሉ የመሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በመቀናጀት መሆን አለበት፣

12. የውሃ መስመር  ዝርጋታ ፣ቅየራ  ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው የመሠረተ ልማት ተቋማት፣-

ሀ. ከመንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ማሰበሪያ ፈቃድ ጠይቆ  ሲፈቀድ ስራውን መሰራት አለበት፣

ለ. ከኢትዮ ተሌኮም፣ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ፣  ከውበትና መናፈሻ   እና ከመሳሰሉት ጋር መረጃ መለዋወጥ በንብረት ላይጉዳት እንዳይደርስ በጥንቃቄ መሆን አለበት፣

ሐ. ከባለስልጣኑ  ውስጥ  ከሚመለከታቸው  የስራ ክፍሎት  ጋር መረጃ መለዋወጥ ይኖርበታል፣

13. የውሃ መስመር ለመዘርጋት፣ለመቀየርና ለመጠገን የሚቆፈረው ጉድጓድ ባለስልጣኑ  ባዘጋጀው ስታንዳርድ እና ወይም በዲያዛይኑ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት የጠበቀ ሆኖ   የሚቆፈረው ጉድጓድ፤-

ሀ. ከአንድ  ቀን በላይ ክፍት ሆኖ መቆየት የለበትም ፣

ለ. የሚተርፍ አፈር ካለ  በሶስት  ቀን ውስጥ መነሳት አለበት፣

ሐ. በዝርጋታው ወቅት በስራ ላይ ስለመኖራቸው በአካባቢው የማስጠንቀቂያ ምልክት መደረግ አለበት፣

መ.  የውሃ መስመር ሲዘረጋ የውሃ መስመር መኖሩን የሚያሳይ የማስጠንቀቂያ   ምልክት /warning  tape / መደረግ አለበት ፤

14. እያንዳንዱ የተዘረጋውና የተቀየረው የውሃ መስመር ከነባር መስመሩ ጋር ተገኛኝቶ አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት መታጠብና በኬሚካል መታከም ይኖርበታል፡፡

15. የመስመር ቅየራ ሲሰራ ከዚህ በፊት የነበረው አሮጌ የቧንቧ መስመር ከነ መለዋወጫው ተሰብስቦ የንብረት አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት ለዚህ ብሎ ባዘጋጀው ቦታ በርክክብ ሰነድ ማስረከብ ይገባል፣

16. የውሃ መስመሩን እንዲቀየር የጠየቀው አካል ወጭውን ይሸፍናል ፣

17. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 2 ተራ ቁጥር 14 እስከ 15የተጠቀሰው የውሃ መስመር ላይ  የቀጠሉ ፤-

ሀ. የውሃ መስመሩን ለማዘወር ወይም ለማሻሻል የጠየቀው አካል የሚቀየረው የውሃ መስመር ላይ ያሉ የደንበኞች የግል ቅጥያ አስከ 3 ሜትር ድረስ ያለውን  ወጪ መሸፈን አለበት፣

ለ. የደንበኛው መስመር ከተዘረጋ ከ10 ዓመት በላይ እና የዘረጋው የውኃ መስመር አይነት ብረት ከሆነ  ወጭውን ደንበኛው መሸፈን አለበት፤

18. የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዙሪያ የውሃ መስመር ዝርጋታ በባለስልጣኑ በራሱ ወይም በሶስተኛ ወገን ሊያሰራ ይቻላል፣

19. የጋራ መኖሪያ ቤቶች የከፍተኛ ፣ የመለስተኛና በሕንጻው ዙሪያ ለሚዘረጋው የውሃ መስመር ወጭውን የሚሸፍነው የህንጻው አሰሪ ይሆናል፣

20. የቁፋሮ እና የሌሎች ግንባታ ሥራዎች የመጨረሻው ክፍያ የሚከፈለው የማጠቃሊያ ሪፖረትና Asbuilt Drawing ከቀረበ በኃላ መሆን አለበት፣

21. በአመት አንድ ጊዜ በውሃ መስመሮች ላይ የተገጠሙትን የውሃ ስርጭት ማሳለጫ መሳሪያዎች ጭምር በመፈተሽ መታጠብና ደህንነቱን የመከታተል ሥራ መሰራት አለበት፡፡

22. የውሃ መስመር ዝርጋታዎች እንደተጠናቀቁ በጥናቱና በዲዛይኑ መሰረት መሰራታቸውን የሚያረጋግጥ ማጠናቀቂያ ሪፖርትና Asbuilt Drawing መሰራትና ጥናቱን ለሰራው የስራ ክፍል እና ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ መላክ አለበት፣

## <u>አንቀፅ 8</u>

## <u>የደንበኞች አገልግሎት ንዑስ የሥራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት</u>

### 1. የውሃ መስመሮች ጥገና ክትትል

1. የውሃ መስመሮች በተለያየ ምክንያት ሲሰበሩ የተሰበረውን መስመር በተቀመጠው የጥገና ጊዜ ስታንዳርድ መሰረት ተጠግኖ ስርጭቱ መቀጠል አለበት፡፡ የሚጠገነው የውሃ መስመር ሌሎች የመሰረተ ልማቶችን የሚያቋርጥ ከሆነ ጥገና ከመሰራቱ በፊት ለሚመለከተው መስሪያቤት በማሳወቅ መረጃ መለዋወጥ አለበት፡፡

2. በባለስልጣኑ የውሃ መስመር ላይ ጉዳት የደረሰው በሶስተኛ ወገን ከሆነ፡-

ሀ. ለጥገናው የተጠቀሙበትን ቧንቧና መገጣጠሚያ ዋጋ፣

ለ. የጉልበት ዋጋ እና ሌሎች ግብአትን ዋጋ፣

ሐ. የፈሰሰው ውሃ ክፍያ /የፈሰሰ ውሃ በሚሰላበት ስሌት መሰረት በማስላት/፣

መ. በጉዳቱ ምክንያት ባለስልጣኑ ያጣው ገቢ ተጣርቶ ጉዳቱ ያደረሰው አካል እንዲከፍል መደረግ አለበት ፣

3. የውሃ መስመር በልዩ ልዩ ምክንያት ከግማሽ ቀን በላይ መቋረጥ የሚያጋጥም ከሆነ በቅድሚያ ለሚመለከተው የስራ ክፍል መሳወቅ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ቁጥር 3 እንደተጠበቀ ሆኖ የመለስተኛ መስመር ከአንድ ቀን በላይ የውሃ አገልግሎቱ ለተቋረጠባቸው ለወረዳውና ለአካባቢው የደንበኞች ፎረም ተወካይ መረጃውን ማሳወቅ አለበት፣
5. የውሃ መስመር ጥገና ስራ ከደንበኛው ወይም ከተለያዩ የከተማው ነዋሪዎች የሚፈስ ውሃ መኖሩን ሪፖረት ሲቀርብ በመስፈርቱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳና ጥራት መሰረት ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

2 .የእሳት አደጋ መቅጃዎች / fire Hydrant/ ተከላ

እሳትና ድንገተኛ የአደጋዎች መካላከያና መቆጣጠሪያ ባለስልጣን ለእሳት ማጥፊያ የሚጠቀምበትን ውሃ ለመቅዳት የሚገለገልበት የእሳት አደጋ መኪኖች ውሃ መቅጃዎች ከመተከላቸው በፊት ከእሳትና ድንገተኛ የአደጋዎች መካላከያና መቆጣጠሪያ ባለስልጣን ጋር በጋራ መቅጃዎቹ የሚተከሉበትን ቦታ መወሰን ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. በአዲስ መልክ የሚዘረጉ የከፍተኛ መስመር እና ከ100 ሚ.ሜ በላይ ያለው የመለስተኛ መስመር ላይ መቅጃዎቹ በመስፈርቱ ወይም በስታንዳርዱ መሰረት መተከል አለባቸው፣

ለ. መቅጃዎቹ የሚተከሉበት የውሃ መስመር ላይ ያለው የውሃ ግፊትም መጠኑ 20 ሜትር ያነሰ መሆን የለበትም ፣

**3.** **የደንበኛ የውሃ መስመር አዲስ ቅጥያና ማሻሻያ**

ሀ. ባለስልጣኑ እስከ ደንበኛው ቤት 12 ሜትር ርቀት ድረስ ውሃ መስመሩን የመዘርጋት ኃላፊነት አለበት ፡፡

ለ. የደንበኛው ቤት ርቀት ከባለስልጣኑ የውሃ መስመር ከ12 ሜትር በላይ ከሆነ ደንበኛው የውሃ መስመሩን ወጭ በመሸፈን አገልግሎት ማግኘት ይችላል፣

ሐ. ከአንድ በላይ የሆኑ ደንበኞች በጋራ የውሃ መስመር መዘርጋት ከፈለጉ ወጭውን ሸፍነው የጋራ መስመር ማዘርጋት ይችላሉ ሆኖም የተዘረጋው መስመር ለተጨማሪ ደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት አቅም ካለው እና አዲስ የውሃ መስመር አገልግሎት ፈላጊዎች ከቀረቡ አገልግሎቱን ለማግኘት ከዚህ መስመር ላይ ለመቀጠል የሚያስፈልጉ ክፍያዎችን አስቀድሞ ለባለስልጣኑ መክፈል ይኖርበታል፡፡

መ. የጋራ መስመር እንዲዘረጋላቸው የሚጠይቁ ደንበኞች የመስመር ዝርጋታው የሚከናወነው የቅ/ጽ/ሥራ አስኪያጆች በአካባቢው የመንግስት መስመር እንደሌለና በቅርብ ቀን መዘርጋት እንደማይችል ሲያረጋግጡና ሲፈቅዱ እንዲሁም ደንበኞች ወጭውን ሸፍነው ለሚያዘረጉት የጋራ መስመር ቧንቧና መገጣጠሚያ ከውጭ የሚገዙ ከሆነም የእቃዎቹ ጥራት በባለስልጣኑ ባለሙያዎች ከታየና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ መሆን አለበት፡፡

ሠ. የደንበኛው የጠየቀው አዲስ ቅጥያም ሆነ ማሻሽያ የውሃ መስመር የቆጣሪ ስፋቱ ከ3/4 ኢንች በላይ ከሆነ ምክንያቱን የቤቱን ሳኒተሪ ኘላን እና ቤቱ ለምን አገልግሎት እንዲሚውል በማስረጃ የተደገፈ ሰነድ በመጨመር ማቅረብ አለበት፡፡

ረ.. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ሀ-ሠ የተጠቀሰው መፈፀም የሚቻለው በደንበኞች አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 11/2012ዓ.ም መሠረት የተቀመጠው መስፈርት ተሟልቶ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

## 4. የደንበኞች ውሃ መስመር ጥገና

ለደንበኞች የግል ቅጥያ እስከ 3 ሜትር ድረስ ያለው የጥገና ወጭ በባለስልጣኑ የሚሸፍን ሲሆን ከ3 ሜትር በላይ ያለውን መስመር የጥገና ወጭ የመሸፈን ኃላፊነት የደንበኛው ይሆናል፡፡

## 5. የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ ቅየራና ጥገና መረጃ አሰባሰብ

ሀ. ሰራውን በማከናወን የማጠናቀቂያ ሪፖርትና Asbuilt Drawing በመሰራት ጥናቱን ለሰራው የስራ ክፍል ያስረክባል፡፡

ለ. በውሃ መስመር ላይ የተሰሩ ስራዎችን በማጠቃለል ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ ይልካል፡፡

ሐ. በዝርጋታ ወቅት የተለወጡ ዲዛይኖችና መገጣጣሚያዎች ካሉ የተቀየረበትን ምክንያት እና ለመለወጡም ተጠያቂ አካል ካለ በመለየት ለማስተካከል የተጠቀመበትን ቢንቢና መገጣጠሚያ  እንዲሁም የተሰራውን ስራ በካርታ ላይ በማስፈር ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ ይልካል፡፡

መ. የአዲስ ደንበኞች መስመር ቅጥያ፣ ማሻሻያ፣ ማዛወሪያ እና ጥገና  የተደረገባቸውን የውሃ መስመሮች፣ መረጃዎች ተሰብስበው ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ መላክ አለበት፣

ሠ. በዋናው መስሪያ ቤት የሚስተዳደርው የከፍተኛ የውሃ መስመር እና በቅ/ጽ/ቤት የሚተዳደረው የመለስተኛ የውሃ መስመር  ሙሉ መረጃዎች ተሰብስበው ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ  መላክ አለበት፣

ረ. በውሃ መስመር ስብራት ምክንያት የፈሰሰ የውሃ መጠን መረጃ በማሰባባሰብ ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ መላክ አለበት ፡፡

## አንቀጽ9

## የውሃ ስርጭት ክትትልና ቁጥጥር

### 1. የውሃ ስርጭት አፈጻጸምና ክትትል ተግባራት

1. የውሃ ስርጭቱ ለማስተካከል ከ125 ሚ.ሜ እና ከዛ በላይ ያሉ ከፍተኛ የውሃ መስመሮች ላይ የተገጠሙ የውሃ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች እና ከማጠራቀሚያ ግቢ ውስጥ ያሉ መለስተኛ የውሃ መስመሮች በዋናው መስሪያቤት በኩል ብቻ ይተዳደራሉ ፣ሆኖም ቅርንጫፎች በመረጃ ልውውጥና በሌሎች በአስፈላጊ ጉዳዮች ዙሪያ ከዋናው መ/ቤት ጋር ተደጋግፈውና ተቀናጅተው ይሰራሉ፡፡
2. የውሃ ስርጭቱ ለማስተካከል ከ110 ሚ.ሜ እና በታች ያሉ መለስተኛ የውሃ መስመሮች ላይ የተገጠሙ የውሃ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ብቻ ይተዳደራሉ፡፡
3. በከፍተኛ የውሃ ማሰራጫ መስመር ላይ የተገጠሙ የውሃ ስርጭት መቆጣጠሪያ/ጌትቫልቮችን/ መሳሪያዎችን ከተመደበው ባለሙያ ውጭ መክፈት ሆነ መዝጋት አይቻልም፡፡
4. በመለስተኛ የውሃ ማሰራጫ መስመር ላይ የተገጠሙ የውሃ ስርጭ መቆጣጠሪያ/ጌትቫልቮችን/ መሳሪያዎችን በዞኑ ከተመደበው ባለሙያ ውጭ መክፈት ሆነ መዝጋት አይቻልም፣
5. ለክትትል ያመች ዘንድ በውሃ ስርጭት መረብ ላይ ለሚገኙ ጌት ቫልቮች የመለያ ስያሜ መሰጠት አለበት፣
6. አመታዊ ፕሮግራም በማዘጋጀት በውሃ ስርጭት መረብ ውስጥ ያሉትን ማንሆሎች ማጽዳትና በውስጡ ያሉትን ጌት ቫልቮች በመፈተሽ ግሪስ መደረግ አለበት፣
7. ለውሃ ስርጭት ማስተካከያ የሚጠቀሙብትን ጌት ቫልቭ ያለበትን ማንሆል በቁልፍ በመዝጋት የተፈቀደለት ባለሙያ ብቻ እንድያስተካክል መደረግ አለበት፣
8. በሲስተሙ ውስጥ ያለውን የውሃ ስርጭት ማስተካከያ ጌት ቫልቭ የመከታተያ ካርድ በማዘጋጀት በተስተካከለበት ጊዜ ሁሉ መረጃው በመመዝገብ ለተጠቃሚው ክፍልም ማሳወቅ አለበት፣
9. የመጠጥ ውሃ  ስርጭት እጥረት ያለበትን አካባቢ በማጥናት / በማስጠናት ተጨማሪ የውሃ አቅርቦት የሚያገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በጀት በመያዝ ተፈጻሚነቱን መከታተል አለበት፡፡
10. አመታዊ የማጠራቀሚያ ጋኖች የአጠባ ፕሮግራም በማዘጋጀት አጠባውን ማካሄድ አለበት፡፡
11. አዲስ ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች ቅጥያ ጥያቄ ሲቀርብ ሲስተሙን አይቶ  መፍቀድ አለበት፣
12. የተገነባውን የሞዴል/ ዲኤምኤ/ DMA/ ወይም በዞን/ በሰብ ሲስተም የተከለለው (Hydraulic Modelling) ወሰን እንዳይጣስ መጠበቅ አለበት፣

13. አንድን ሲስተም የሚጋሩ ቅ/ጽ/ቤቶች ዘንድ በውሃ አቅርቦት ምክንያት አለመግባባት ከተፈጠረ ለችግሩ መፍትሄ የሚሰጠው በዋናው መ/ቤት በኩል ነው፡፡

14. ወደ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚላከውን የውሃ መጠን በመወሰን እና መረጃ በመያዝ ለሚመለከተውም ዘርፍ በማሳወቅ ተግባራዊነቱን መከታተል አለበት፣

15. የአካባቢውን የውሃ ሽፋን/ water coverge/ በየግዜው (በተለይም በምርት ላይ ችግር ሲያጋጥም )በማውጣት ክፍተት ሲኖር የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት፣

16. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስርጭት ችግር ላለበት አከባቢ ውሃ በቦቴ በመሙላት በአካባቢው በተተከሉት ሮቶዎች አማካኝነት ማሰራጨት አለበት፣

17. በተለያዩ ምክንያቶች የውሃ ስርጭት ለጊዜው ሲቋረጥ ውሃ በቦቴ ለአካባቢው ነዋሪ በተንቀሳቃሽ ቦኖ መልክ መታደል አለበት፣

18. ቅ/ጽቤት የውሃ ስርጭቱን ሳይቆራረጥ ለማዳረስ ካልተቻለ በአካባቢው የደረሰውን የውሃ መጠን መቀነስ ታሳቢ በማድረግ ፍትሀዊ በሆነ ሁኔታ ውሃ በፈረቃ የሚሰራጭበትን ፕሮግራም በማዘጋጀትና በማሳወቅ ተግባራዊነቱን መከታተል አለበት፣

19. የውሃ ስርጭት ችግር ያለበት አካባቢ የፈረቃ ፕሮግራም በማውጣት ለአካባቢው ነዋሪዎች በማሳወቅ ፍትሃዊ የሆነ ክፍፍል እንዲኖር መደረግ አለበት፡፡

20. የየእለቱን የውሃ ስርጭት መረጃ ቢያንስ በቀን ሁለት ግዜ በማሰባሰብ ለሚመለከተው ክፍል ማሳወቅ እና መፍትሄ የሚያስፈልገው ከሆነም ተከታትሎ መፍታት አለበት፡፡

21. በልዩ ልዩ ምክንያት የውሃ ሥርጭቱ ከግማሽ ቀን በላይ የሚቋረጥ ከሆነ በቅድሚያ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ማሳወቅ አለበት፡፡

22. የውሃ ሥርጭት ሲስተሙ እንዳይስተጓጎል ለማድረግ በየግፊት መስጨያ ጣቢያዎች ለሀይል መጠባበቂያ የተቀመጡትን ጀነሬተሮች ደህንነታቸውን በመጠበቅ እና የነዳጅ አቅርቦትም በመከታተል እንዲሞላ በማድረግ እንዲሁም የግፊት መስጭያ ጣቢያዎችን ኤሌትሪክ ሀይል አቅርቦት በመከታተል የሃይል መቆራረጥ ሲከሰትም ለሀይል መጠባበቂያ የተቀመጠውን ጀነሬተር በማስነሳት የውሃ ስርጭት እንዳይቋረጥ መደረግ አለበት፡፡

23. ፍትሀዊ የውሃ ሥርጭት እንዲኖር ለማድረግ በሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት የግፊት መስጫ ፓምፖችን ማሰራት አለበት፡፡

24. ወደ ማጠራቀሚያዎች ገቢና ወጭ የውሃ መስመሮች ላይ የተተከሉትን የውሃ ስርጭት ማሳለጫ መሳሪያዎች በአመት አራት ጊዜ ፍተሻ በማድረግ የማስተካከያ እና የጥገና ስራ መከናወን አለበት፡፡

25. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 24 የተያለው እንደተጠበቀ ሆኖ የግፊት መስጭያ ጣቢያ ላይ የተተከሉትን ለውሃ ስርጭቱ ማሳለጫ የሚሆኑ መሳሪያዎች በትክክል መስራታቸውን

በማረጋገጥ፣በመከታተል የሰሩበትን ሰዓት መረጃ በመሰብሰብ  እና መዝግቦ ማደራጀት ቅ/ጽ/ቤት እንዲያውቁት መደረግ አለበት፣

26. የግፊት መስጫ ፓምፖችን፣ ጀነሬተሮችን እና ለስራው የሚያስፈልጉ ንብረቶችን ተረክበው በማስተዳደር ደህንነቱንና ንፅህናውን መጠበቅ አለበት፣

27. ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የውሃ ስርጭት ሁኔታን እና የውሃ ስርጭት ላይ ችግር ሲያጋጥም መረጃውን ለክፍለ ከተማ አመራሮች፣ ለወረዳ አመራሮች፣ ለወረዳ የማህበረሰብ ተሣትፎ ጽ/ቤት፣ ለደንበኛ ፎረም አባላት እና ከደንበኞች ለተመረጡ ፎካል ሰዎች በየጊዜው ማሳወቅ አለበት፡፡

28. ለውሃ ስርጭት መቆራረጥ ምክንያት ከሚሆኑት ወሣኝ ምክንያቶች አንዱ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት በመሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዞናቸው ከሚገኝ የኤሌትክሪክ አገልግሎት ጽ/ቤትና ከአስቸኳይ ጥገና ቡድን ጋር ተቀናጅተው መስራት አለባቸው፡፡

29. የውሃ ስርጭት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ እና በውሃ መስመሮች እና ቫልቮች ላይ ያልተገባ ወይም ህገወጥ የሆነ መነካካት፣ ግንባታ እና ስብራት እንዳያጋጥምና ሲያጋጥምም ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ያመች ዘንድ ከክልላቸው ፖሊስ እና ደንብ ማስከበር ጋር ተቆራኝተው መስራት አለባቸው፡፡

**2. የውሃ ሥርጭት የመረጃ አሰባሰብ**

1. በየእለቱ በማጠራቀሚያ ፣ በግፊት መስጭያ ጣቢያና በዋና ዋና መስመሮች ላይ ከተተከሉት መሳሪያዎች/ወይም የውሃ ቆጣሪዎች ላይ መረጃዎቹን በመሰብሰብ እና መተንተን  የውሃ ስርጭት ላይ ክፍተት ሲኖር ለማስተካከል መጠቀም አለበት የተለየ ችግር ሲያጋጥምም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለችግሩ የሚመጥን መፍትሄ መስጠት አለበት፣
2. ከማጠራቀሚያዎች እና የግፊት መስጭያ ጣቢያዎች  የተሰበሰቡትን ዕለታዊ መረጃዎች በማጠናቀር ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ  መላክ አለበት፣
3. የውሃ ስርጭቱ ሳይቆራረጥ ለ 24 ሰዓት እና በፈረቃ ውሃ የሚያገኙትን አካባቢዎች እና ያለውን የውሃ አቅርቦት ወቅታዊ አድርጎ ካርታ ላይ በማስፈር በየቅርንጫፉ ክልል እና በየወረዳው ያለውን የውሃ ስርጭት ዝርዝር ሁኔታ በየወሩ በማሰባሰብ ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ  መላክ አለበት፣

## አንቀጽ10

## ገቢ የማይሰበሰብበት ውሃ ለመቀነስ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር

**1. የውሃ ብክነት ምርመራ እና ቁጥጥር**

1. በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት ዋናው መስሪያቤትም ሆነ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚያስተዳድራቸው የውሃ መስመሮች ላይ በዓይን የማይታይ ብክነትን ለማግኘት በብክነት መመርመሪያ መሣሪያዎች በመታገዝ የውሃ ብክነትን ያስከተለውን የውሃ መስመር ስብራቶች በመለየት እንዲጠገኑ መደረግ አለበት፡፡
2. ቅድመ ቅየራ እና ጥገና መረጃዎችን በመሰብሰብና በማደራጀት መቀየር ያለባቸውን የውሃ መስመሮች ኢንዲቀየሩ ለመድረግ የሚያስችል ዝርዝር የጥትና ዲዛይን ሥራ መስራት አለበት፡፡
3. ፕሮግራም በማውጣት የውሃ መስመሮች የተዘረጉበትን ቦታ በመፈተሽ በአይን የሚታይ የውሃ ብክነት መኖሩን እና አለመኖሩን መከታተል ብክነት የተገኘበት መስመር እንዲጠገን መደረግ አለበት፡፡
4. በአይን የሚታይና የማይታይ የውሃ ብክነት የተገኘበት የውሃ መስመር፣ የቦታው ልዩ ስም ና /X,Y,Z/ ፣ከብክነት የዳነ የውሃ መጠን እንዲሁም የውሃ መስመሩ ላይ የተሰራውን የጥገና አይነት በመግለጽ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መረጃዎችን በማደራጀት ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ መላክ አለበት፡፡

**2. የውሃ ኦዲት ስራዎች**

1. ከገፀ ምድር እና ከርስ ምድር የውሃ ምርት መገኛ ጣቢያዎች በየዕለቱ የምርት መጠን ልኬት መረጃ መሰብሰብ አለበት፣
2. የውሃ ኦዲት ለመስራት የሚያስፈልጉ በመስፈርቱ ላይ የተቀመጡ መረጃዎችን ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት በየወሩ፡-
   - ሀ. በቦቴ የተቀዳ ፣የተሸጠና በነጻ የተሰጠውን የውሃ መጠን በመለየት፣
   - ለ. የእሳትና ድንገተኛ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር የተጠቀመበትን የውሃ መጠን፣
   - ሐ. ማጠራቀሚያ እና የውሃ መስመር የታጠበበትን የውሃ መጠን፣
   - መ. ባለስልጣኑ በሚያስተዳደራቸው በተለያዩ ቦታዎች አገልግሎት ላይ እየዋለ በቢል ላይ የማይወጣ የውሃ መጠን፣
   - ሠ. በተለያዩ ምክንያቶች በውሃ መስመር ላይ የፈሰሰውን እንዲሁም ክፍያ የተከፈለበትንና ያልተከፈለበትን የውሃ መጠን በመለየት፣

ረ. በቢል ላይ የሚወጣ የውሃ መጠን ፣ በተለያየ ምክንያት በታረሙ ቢሎች ውድቅ የተደረጉ የውሃ ፍጆታ ቢሎች እና ክፍያ የተከፈለበት የውሃ መጠን መረጃ በማሰባሰብ መደራጀት አለበት፣

3. በተለያዩ ጥናቶች የተወሰነውን አንድ ሰው በቀን ማግኘት ያለበትን የውሃ ፍጆታ በትክክል ማግኘቱን ማረጋገጥና ልዩነቱን በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡/ለዚህም አሰራር ሲባል የከተማውን የህዝብ ቁጥር መረጃ ከሚመለከተው አካል በመውሰድ ወቅታዊ የሆነ መረጃ መጠቀም ይገባል/
4. ደንበኞችን በውሃ አጠቃቀም ለይቶ በማወቅና ጥቅም ላይ ውሎ ገንዘብ የማይሰበስብበት የውሃ መጠን ለመቀነስ፡-

   ሀ. ከ 0-14 ሜትር ኩብ ያለውን በዝቅተኛ ተጠቃሚ፣

   ለ. ከ14-100 ሜትር ኩብ ያለው መካከለኛ ተጠቃሚ፣

   ሐ. ከ101 ሜትር ኩብ በላይ እና የውሃ ቆጣሪ ስፋቱ ከ1¼ ኢንች /32 ሚ.ሜ/ በላይ የተቀጠለላቸው ደንበኞች ከፍተኛ ተጠቃሚ በማለት መከፋፈል አለበት፣
5. የከፍተኛ ተጠቃሚዎች በየወሩ የሚጠቀሙበትን የውሃ ፍጆታ መጠን የሚገልጽ መረጃ በመሰብሰብ፣ በማጥናት፣ በመተንተን የደንበኞችን አይነት እና የውሃ ቆጣሪያቸውን ከሚጠቀሙበት የውሃ ፍጆታ መጠን ጋር የማጣጣም እና የመከለስ ስራ መሰራት አለበት፣
6. የደንበኞችን የውሃ አጠቃቀም ከዚህ በታች በተዘረዘረው ፡-

   ሀ. ለሻወር አገልግሎት ጭምር የሚጠቀሙበት፣

   ለ. አንድ አባወራ በባሊ ብቻ የሚጠቀምበት ፣

   ሐ. ከሁለት አባወራ በላይ የሚጠቀሙበት ፣

   መ. ለእንዱስትሪ አገልግሎት የሚውለውን፣

   ለ. ለተቋም አገልግሎት የሚውለውን/ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ/

   ሠ. ለንግድ አገልግሎት የሚውለውን (ለሆቴል፣ለካፌ፣....)

   ረ. ለቦኖ አገልግሎት የሚውሉ በማለት በመለየት የነባርም ሆነ አዳዲስ ደንበኞችን መረጃ በመሰብሰብ መደራጃት አለበት፡፡
7. የተመረተው የውሃ መጠን ጥቅም ላይ የዋለውንና ያልዋለውን በመለየት በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በየሩብ ዓመቱ ማሳያ በመስራት ዓመታዊ የተጠቃለለ የውሃ ብክነት ስሌት መስራት አለበት፣
8. ልዩ ልዩ ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ማንዋሎችንና የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾችን በማዘጋጀት በስራ ላይ እንዲውሉ መደረግ አለበት ፣

9. የሲስተሙን የውሃ ግፊት /ፕሬዠር/ ለማወቅና ለመለካት የመለኪያ ቦታ እንዲዘጋጅ መደረግ አለበት ፣

10. በየአመቱ የባለስልጣኑን የፋይናንስ እንቅስቃሴ (financial balance sheet) መረጃ በማሰባሰብ እና ገንዘብ የማይሰበሰብበትን የውሃ መጠን ለመቀነስ የሚወጣውን ወጭ እና የባከነው የውሃ መጠን በገንዘብ ማስላት አዋጭነቱን አይቶ ለቀጣይ ተግባር አሰራር መንደፍ አለበት፣

11. ወደ ቅ/ጽ/ቤት ክልል የሚገባውን የውሃ መጠንና እና በቅ/ጽ/ቤቱ ክልል በውስጥ ያሉትን የደንበኞች የውሃ ፍጆታ / በውሃ ቆጣሪ የተነበበው የፍጆታ መረጃ መሰረት / መረጃዎች በመሰብሰብና በመተንተን በቅ/ጽ/ቤቱ ክልል ውስጥ ያለው ገቢ የማይሰበሰብበትን የውሃ መጠን በማስላት ተገቢውን እርምጃ መውስድ አለበት ፣

## 3. የቆጣሪ ነክ ሥራዎች አፈጻጸም

1. የቆጣሪ መመርመሪያ መሳሪያዎች ልኬት፣ ፍተሻ እና ደህንነት በመከታተል ቀላል ጥገና እና መለዋወጫ መቀየር አለበት፣
2. የባለስልጣኑ ደንበኞች የተጠቀሙበትን የውሃ መለኪያ /የውሃ ቆጣሪ /ከመተከሉ በፊት ምርመራ በማድረግ ውጤቱ መተንተን አለበት ፣
3. አገልግሎት ሰጥተው የተነሱ ቆጣሪዎችን መልሶ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ የማጽዳት፣ ቀለም የመቀባትና ጥገና የሚያስፈልጋቸውንም የማስተካከል ስራዎችን በመስራት ለዚህ ስራ የወጣውን ወጭ በመተንተን መደራጀት አለበት፣
4. የተመረመሩ ቆጣሪዎች መረጃ በማደራጀትና በመተንተን ፡-
   ሀ. በውሃ ስርጭት ሲስተም መረብ ላይና ለደንበኞች ለመቀጠል የሚያስፈልገውን የአዲስ ቆጣሪ ግዢ ዝርዝር መስፈርት በማዘጋጀት ግዥው እንዲፈጸም መደረግ ይኖርበታል፣

   ለ. ጥቅም ላይ የዋለ ነገር ግን በቆጣሪ ጥራት ችግር ምክንያት የሚፈጠረውን ገንዘብ የማይሰበሰብበትን የውሃ መጠን ለመቀነስ የሚረዳ ሀሳብ ማቅረብ ይኖርበታል፣

   ሐ. የቆጣሪ አስተዳደር ፖሊሲ በማዘጋጀትና በማፀደቅ ተግባራዊነቱን መከታታል ይኖርበታል፣

   መ. የውሃ ቆጣሪዎችን ጥራት ለመጠበቅ የሚረዱ አጠቃቀም ስልቶችን በመንደፍ ለዚህ የሚረዳ የአሰራር ማንዋል መዘጋጀት ይኖርበታል ፣

   ሠ. የተመረመሩ ቆጣሪዎችን የምርመራ ውጤት በቆጣሪ ቁጥርና በስፋታቸው፣ የተነሱበትን አድራሻ፣ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ካጋጠመው ችግር ጋር በማደራጀት መረጃው ተሰብስቦ ለማዕከላዊ መረጃ ቋት መላክ አለበት፡፡

5. በየቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተለያየ ምክንያት የቆሙና ችግር የደረሰባቸው እስከ 1½ ኢንች /40 ሚ.ሜ/ ድረስ ያሉትን የደንበኞች የውሃ ቆጣሪዎች በማንሳት በመስፈርቱ መሰረት መመርመር ይኖርበታል፣
6. በዋናው መስሪያቤት በተለያየ ምክንያት የቆሙና ችግር የደረሰባቸው ከሁለት እስከ 12 ኢንች /50 -300 ሚ.ሜ/ ድረስ የሆኑትን የደንበኞች የውሃ ቆጣሪዎች በማንሳት በመስፈርቱ መሰረት መመርመር ይኖርበታል፣
7. በተደረገው ምርመራ ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ መሆናቸው የተረጋገጡ የውሃ ቆጣሪዎች ተለይተው በህግ አግባብ ለማስወገድ እዲቻል ለንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት በሰነድ ርክክብ መፈጸም ይኖርበታል፣

**4. የዲኤምኤ /DMA/ District Metered Areas/ እና ዞን ክፍፍል**

**በአዲስ እና በነባር የዲኤምኤ /DMA/ ዞን**

1. ዲኤምኤ /DMA/ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል በተቀመጠለት መስፈርት መሰረት ክፍፍሉ የሚሰራ ሆኖ ዞን/ሰብ ሲስተምና ሴክተር በዋናው መስሪያ ቤት በኩል በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የክፍፍሉ ስራ መሰራት ይኖርበታል፣
2. የዲኤምኤ /DMA/ District Metered Areas/ እና ዞን ክፍፍል ሲደረግ የገቢና ወጭ የውሃ መስመሮች ላይ የውሃ ና የግፊት መጠንና መለኪያ መሳሪያ መገጠም ይኖርበታል፣
3. ለየዞኑ የሚሰጡ የከርሰ ምድር የውሃ ምርት የሚገኝበትን ጉድጓዶችንና ምንጮች፣ ማጠራቀሚያዎችና ግፊት መስጭያ ጣቢያዎችን ፣የውሃ መስመሮችንና በላያቸው ላይ የተገጠሙትን የውሃ ስርጭት ማሳለጫ መሳሪያዎችን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ሙሉ መረጃውን በማደራጀት ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ መላክ አለበት፣
4. በክፍፍሉ ውስጥ ያሉት የውሃ መስመሮች ፣ጌት ቫልቮች፣ሃይድራንቶች እና የግፊት መቀነሻ ቫልቮችን በመፈተሸና በማስተካከል ወቅታዊ በማድረግ እንዲሁም በውስጡ ያሉት ደንበኞች በአይነትና በቁጥር ለይቶ መያዝ ይኖርበታል፣
5. የውሃ ሲስተሙን ማሳላጫ መሳሪያዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ የማንሆል መገንባት ይኖርበታል
6. በተከፋፈለው በዞን /ሰብሲስተም እና ሴክተር ላይ የውሃ ኦዲት በመስራት ገንዘብ የማይሰበሰብበት የውሃ መጠን ከፍተኛ የሆነበትን አካባቢ በመለየት ዲኤምኤ /DMA/ ሥራ ከቅ/ጽ/ቤት ጋር በጋራ አካባቢውን መለየት አለበት፣
7. ገቢ የማይሰበሰብበት ጥቅም ላይ የዋለውንና ያልዋለውን የውሃ መጠን በየአይነት ለመለየት እንዲቻል ሰብ ሲስተሞቹ በውስጣቸው ከያዙት የደንበኞች የውሃ ቆጣሪ ውስጥ በናሙና መልክ እስከ 5 በመቶ የሚደርሱትን በማንሳት መመርመር ይኖርበታል ፣

8. ውሃ የሚያባክነው የወሃ መስመር ለመለየት በዲኤምኤ /DMA/ ውስጥ ያሉት መለስተኛ እና ከፍተኛ ደንበኞች መስመር ጭምር በብክነት መፈተሻ መሳሪያ በመታገዝ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አሳሳ መደረግ አለበት፣ ግኝቱም መተንተን ይኖርበታል፣
9. በሚሰራው የዲኤምኤ /DMA/ ላይ እንዲደረስበት የሚፈለገው ገንዘብ የማይሰበሰብበት የውሃ መጠን እስኪ ደርስ ድረስ በመደጋገም መሰራት ይኖርበታል፣
10. .በሚሰራው የዲኤምኤ /DMA/ ላይ በአይን የሚታይ እና የማይታይ የውሃ ብክነት የተገኘበት የውሃ መስመር፤ የተሰራው ሥራ፣ የጥገና አይነት ፣ የቦታው ልዩ ስምና /X,Y,Z/ ጨምሮ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መረጃ አሰባስቦ በመያዝ ለቀጣይ ሥራ እንዲረዳ ለማዕከላዊ መረጃ ቋት ማደራጃ መላክ ይኖርበታል፣
11. በተከለሉ የዲኤም /DMA/ እና ዞን ክልል ውስጥ አዲስ ቅጥያ፣ማሻሻያ እና ከደንበኛ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ሥራዎች ሲሰሩም መረጃው መቅታዊ መደረግ ይኖርበታል፣
12. የተከለሉ ዲኤምኤ/DMA/ እና ዞን በአመት አራት ጊዜ ደህንነታቸውን በመከታተል በአይን የሚታይም ሆነ የማይታይ የውሃ ብክነት መኖሩን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የማጣራትና የማስተካከል ሥራ መከናወን ይሮርበታል ፣
13. የተከፋፈሉት ዞኖች ውስጥ ያለው የውሃ ግፊት /Average Operating Pressure/ መጠን መረጃ ወቅታዊ መደረግ ይኖርበታል ፣
14. በውሃ ስርጭቱ ሲስተምና እና ገንዘብ የማይሰበሰብበት የውሃ መጠን ቅነሳ ላይ ክትትሉ ያመጣውን ውጤት በዋናው መስሪያ ቤትና በቅ/ጽ/ቤት ሀላፊዎች ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ መገምገም ይኖርበታል።

## 5. ማዕከላዊ የመረጃ ማጠናቀሪያና ማደራጃ

1. አጠቃላይ የባለስልጣኑ የውሃ መሰረተ ልማት መረጃ የግንባታው አይነት፣የተገነባበት ዘመን ፣ጥቅሙን እና የመሳሰሉትን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሰራር በመጠቀም ወጥነት ባለው መልኩ መደራጀት ይኖርበታል።
2. የባለስልጣኑ የውሃ ደንበኞች ሙሉ መረጃ ወቅታዊ በማድረግ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሰራር በመጠቀም ወጥነት ባለው መልኩ መደራጀት ይኖርበታል።
3. በዋናው መስሪያ ቤት ፣በቅ/ጽ/ቤት እና በፕሮጀክት ጽ/ቤት በየበጀት አመቱ የታቀዱትንና የተሰሩትን የውሃ መሰረተ ልማቶች መረጃ በማሰባሰብና መረጃውን ወቅታዊ በማድረግ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሰራር በመጠቀም ወጥነት ባለው መልኩ መደራጀት ይኖርበታል።

4. በአይን የሚታይ እና የማይታይ የውሃ ብክነት የተገኘበት የውሃ መስመር፤የተሰራው ሥራ፣ የጥገና አይነት ፣ የቦታውን ልዩ ስም /X,Y,Z/ ጨምሮ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መረጃዎቹን ከመስክ ከሚሰበስቡት የስራ ክፍሎች በመረከብ ለቀጣይ ተግባራት ይረዳ ዘንድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሰራር በመጠቀም ወጥነት ባለው መልኩ መደራጀት ይኖርበታል።

5. ከየስራ ክፍሉ በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ በመንተራስ ወቅታዊ የውሃ ስርጭትን የሚያሳይ ካርታ መስራት አለበት፣

6. መረጃዎችን ለማግኘት የባለስልጣኑ የስራ ክፍሎችም ሆነ ከባለስልጣኑ ውጭ የሆኑና አግባብ ባለው የባለስልጣኑ የስራ ሃላፊ መረጃውን እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች ወይም ሰዎች በሚጠይቁበት ጊዜ ወቅታዊና ትክክለኛ የውሃ መሰረት ልማት መረጃዎችን መስጠት አለበት።

## 6. የውሃ አጠቃቀም ትምህርት እና ውሃ ቆጣቢ መሳሪያዎች ስርፀት

1. በውሃ መገኛዎች፣ ማጠራቀሚያዎች፣የግፊት መስጫ ጣቢያ፣ የውሃ ብክነትና ብክለት መከላከል ስልትን ለሚመለከታቸው ሰራተኞችና ደንበኞች ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት አለበት፣
2. በየበጀት አመቱ እቅድ በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ስለውሃ አጠቃቀምና አያያዝ ስልጠናና ትምህርት መስጠት አለበት፣
3. ለደንበኞች በተለይ ለከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚዎች በየጊዜው ክትትል በማድረግ የውሃ አጠቃቀማቸውን መረጃ በመሰብሰብ የውሃ ቆጣቢ መሳሪያዎችን እዲጠቀሙ የተለያዩ መሳሪያዎችን ማሳየት እና ግንዛቤ መስጠት አለበት፣
4. በየስራ ክፍሉ ለተመደቡ ነባርና አዳዲስ ሠራተኞች የብክነት መፈለጊያ መሣሪያዎች ሥልጠና መስጠትና የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ ይኖርበታል ፣
5. ዘመኑ የደረሰበትን ወቅታዊ የውሃ ብክነትና ብክለት መከታተያና መከላከያ ቴክኖሎጂ እና ውሃ ቆጣቢ መሳሪያዎችን አቅም ባገናዘበ መልኩ ተገዝተው ስራ ላይ እንዲውሉ ጠቀሜታውን ለሚመለከተው አካል ግንዛቤ ማስጨበጥ መስጠት አለበት ፣
6. ከማምረቱ ጀምሮ እስከ ተጠቃሚው ያለውን የውሃ ስርጭት ሁኔታ ለህብረተሰቡ ትምህርት በመስጠት የውሃ አጠቃቀማቸውን እንዲስተካክሉ ግንዛቤ መስጠት አለበት፣

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀፅ 11
## ተጠያቂነት

1. በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጣለበትን ሃላፊነት በአግባቡ ያልተወጣ የሥራ መሪ / ሰራተኛ በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብና በህብረት ስምምነት መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. በዚህ መመሪያ የውስጥ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣና የሐሰት ማስረጃ ያቀረበ ደንበኛ አግባብ ባላቸው የባለስልጣኑ መመሪያዎችና የሃገሪቱ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡
3. የዚህን መመሪያ አፈፃፀም ያደናቀፈ ወይም ትርጉሙን እና አሰራሩን ያዛባ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊና ሰራተኛ በፍ/ብሔርና የወንጀል ህግ ያለው ተጠያቂነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ በህብረት ስምምነቱ እና በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተገቢው የዲሲፐሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## አንቀጽ12
## ክልከላ

1. ከተፈቀደላቸው የባለስልጣኑ ባለሙያዎች ውጭ በውሃ መስመሮች ላይ የተገጠሙ መዝጊያና መክፈቻ /ጌትቫልቮችን/ ሲነካካ የተገኘ ሰው በሀገሪቱ ህግ መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል፣
2. በውሃ መስመሮች እና በማንሆሎች ላይ ምንም አይነት ግንባታ ማከናወን የተከለከለ ነው
3. ባለስልጣኑ በሚጠቀምባቸው የውሃ ምርት መገኛ አካባቢዎች ላይ መርዛማ ኬሚካል፣ነዳጅ እና የመሳሰሉትን ማፍሰስ የተከለከለ ነው፡፡
4. የውሃ ማጣሪያ ጣቢያ ፣ግፊት መስጭያ እና የውሃ ጉድጓዶች አካባቢ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ውጭ መግባትም ሆነ ማደር የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀፅ 13
## መመሪያውን የማሳወቅ ግዴታ

ማንኛውም የባለስልጣኑ ሃላፊ ፣የሥራ ክፍልእና ሰራተኛ የሚመለከታቸውን አካላት እና የባለስልጣኑ ደንበኞች ስለመመሪያው አፈፃፀም በቂ እውቀት እንዲኖራቸው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀፅ 14

## የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በየትኛውም ደረጃ ያሉ የባለስልጣኑ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች ፣ የሚመለከታቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ህግና ደንብ እንዲያስከብሩ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት፣ ማንኛውም ሰው እና ደንበኞች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 15

## ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች ወይም አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀፅ 16

## መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 17

## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተፈርሞና የባለሥልጣኑ ማህተም ካረፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አቶ አወቀ ኃ/ማሪያም

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

ዋና ሥራ አስኪያጅ